በምስጢር የሚያዝ □ □ □ □

# ስለ ቀጣዩ ምርጫ

በዚህ ጉዳይ ተወያይተን መመለስ ያለብን ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ። መጀመሪያ ምን አቋዋም ይኑረን የሚለው ጥያቄ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የያዝነውን አቋዋም ብንይዝ በዚህ ዙሪያ በውጭም በውስጥም እንዴት ነው የ ምንንቀሳቀሰው? የሚለው ጥያቄ ይሆናል።

## አንደኛ ጥያቄ - ምን አቋዋም እንያዝ?

መነሻ ነጥባችን። ደግመን ደጋግመን የኢህአዴግ መንግስት በህዝባዊ ትግል ተገዶ ዴሞክራሲ በሃገራችን እስካ ልሰፈነ ድረስ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ሊካሄድ አይችልም ብለናል። ይህ እስካልሆነ ድረስ ከቀጣዩም ሆነ ከዚያ ሊከተሉ ከሚችሉት ምርጫዎች አንፃር እኛም የኢትዮኦያም ህዝብ ምንም የምንጠብቀው ነገር አይኖርም። መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች ኢህአዴግ ምርጫ እያለ በየ አምስት አመቱ የሚያዘጋጀውን ንልት ይህንን የምንመኘውን ህዝባዊ እንቅስቃሴ መነሳሳት ልናግዝበት እንችላለን ወይ? ይህ እንዲሆን ደግሞ ምን ማድረግ አለብን የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው።

1ኛ የዚህ "ምርጫ" ውጤት ከወዲሁ የታወቀ ስለመሆኑ። በአለፈው ምርጫ ነፃ ፕሬስ፣ ከምላ ጎደል ቢሆንም የመደራጀት፣ ቅስቀሳ የማካሄድ መብቶች ነበሩ። ኢህአዴግ ራሱ "እንከን የለሽ ምርጫ ይሆናል ያሻህን ምረጥ ሲልና ከተቃዋሚዎች እኩል ቤት ገብቶ በህዝብ ፊት በቴሌቪዥንና ሬድዮ ሲከራከር የታየበት ሁኔታ ነበር። ተቃዋሚዎችም ከሞላ ጎደል በአንድነት ቆመው ውጣና ድምፅህን ስጥ ካሸነፍን የጋራ መንግስት እናቋዋቁማለን እስከማለት ሄደውና ከተ ጭበረበረ ደግሞ በትግል ድልህን እናስከብራለን ብለው ሰፊና ተአማኒነት የነበረው ቅስቀሳ አድርገው ነበር። አለም አቀ ፋም ኮሚኒቲ የምርጫውን ነፃና ርትአዊ መሆን አረጋግጣለሁ ብሎ ከዚህ በፊት ባልታየ ብዛት ታዛቢዎችን ለአንድ ለሁ ለት ሳምንት የምርጫ ሰሞን ብቻ ሳይሆን ሁለት ወር ያህል በሃገሪቱ አሰማርቶ ነበር። በነዚህ ሶስት "አጋቹ ክስተቶች" በመጠቀም ህዝባችን ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ ድል አደረገ። ሆኖም በተለይ የምርጫ ቦርዱ ላይ ባለው ሙሉ ቁጥጥ ር በመጠቀምና በገፍ በማጭበርበር ኢህአዴግ በአሸናፊነት ወጣሁ አለ። ከዚያ ወዲህ የሆነውን፣ ድምፄ ይከበር ባለው ህዝብ ላይ የተፈፀመውን ግፍ፣ የተከፈለውን መስዋእትነት የምናውቀው ነው።

2ኛ አሁን በአለው ሁኔታ ህዝባችን የኢህአዴግ "እንከን የለሽ" ምርጫ ነገር ቅጥፈት እንደሆነ፣ በኢህአዴግ ስ ር ምን ቢሆን ምን ነፃ ምርጫ የሚሉ ነገር እንደማይኖር ጠንቅቆ ያውቃል። በዚህ ላይ ደግሞ በተቃዋሚዎች ላይ ጨር ሶ እምነት በማጣቱ ከምርጫ አንዳች ነገር አገኛለሁ ብሎ የማያምን ህዝብ ነው። ይህ ስለተባለ ግን በምርጫው አይሳተ ፍም ማለት አይደለም። እንደማንኛውም ቶታሊታያን አገዛዞች ስር ያለ ህዝብ የግዱን ወጥቶ ድምፁን ይሰጣል። ግንቦት 97 ህዝባችን ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በምርጫ እምነት ስለነበረው ከመራጩ ህዝብ 82.6% ድምፁን ሰጥቱዋል ። ዛሬ ምርጫ በሚሉ ነገር ጨርሶ እምነት የአጣ መሆኑን እያወቅነውና ከተቃዋሚዎችም አንዳንዶቹ ሂደቱን ቦይኮት ባ ደረጉበት ሁኔታ በአለፈው አመት በተደረገው ምርጫ ከተመዘገበው ህዝብ 93% ድምፁን ሰጥቱዋል ኢህአዴግ ለውድ ድር ከቀረቡት መቀመጫዎች 97% አሸነፈ ተብለናል። የ2002 ምርጫም በሂደቱም፣ በተሳትፎውም፣ በውጤቱም ከአ ምናው የተለየ አይሆንም።

3ኛ. በዚህ ሁኔታ ለሃገራችን ዴሞክራቶች ያሉት ሶስት አማራጮች አንደኛ የቦይኮት ጥሪ ማድረግ፣ ሁለተኛ ተ ሳትፈው አህአዴግ የሚወስንላቸውን የመቀመጫ ልክ መቀበልና ሶስተኛ ደግሞ በምርጫው ዘመቻ ተሳትፎ በመጨረሻ ው ደቂቃ ከሂደቱ ራስን ማግለል ናቸው። ሶስቱም አማራጮች "ከዚያስ?" ከምትለው ወሳኝ ጥያቄ ጋር አብረው ካልታ ዩ የትም የሚያደርሱ ስለአይደሉ ስለነዚህ አማራጮች ምንነትና በቀጣዩ ትግል ላይ ስለሚኖራቸው ጫና ዘርዘር አድርገ ን መወያየት ይኖርብናል።

ሀ/ አንደኛው አማራጭ የቦይኮት ጥሪ ማድረግ። ግንቦት 97 ይህንን አማራጭ ስናሰላስል "ቦይኮት ከተደረገ እ
ኛ ብቻ ሳንሆን ህዝባችንን ይዘን" የሚል አካሄድ ነበረን። "ህዝባችንን ይዘን" የሚለው አቁዋም የሚደረገው ቦይኮት በ
ገፍ በሆነ፣ አለም በግልፅ በሚያየው፣ ህዝባችንም ሃያል መሆኑን በሚያሳይ መልክ ይካሄድ ማለት ብቻ አልነበረም። ህ
ዝባችን በዚህ መልክ በግልፅና በገፍ ይህንን ንልት አሻፈረኝ ከአለ በዚያው እምርታ ለነፃ ምርጫ መንገድ የሚጠርግበት
ን ትግል ሳያሰልስ የሚቀጥልበትም ሁኔታ እናመቻቻለን የሚል እቅድ ነበረን። አሁን ከላይ በተወሳው ምክንያት ህዝባች
ን በገፍና ቀልብ በሚስብ መልክ ምርጫውን ቦይኮት የሚያደርግበት ሁኔታ የለም። ዞሮ ዞሮ ደግሞ ከዚህ ምርጫ ታማ
ኝ ተቃዋሚዎች የተወሰነ መቀመጫ ስለሚሰጣቸውና ፓርላማ ስለሚገቡ "መድበለ ፓርቲ ምርጫ ተደርጎ ኢህአዴግ አ
ሸነፈ ተቃዋሚዎችም የማይናቅ የወንበር ቁጥር የያዙበት ፓርላማ ተሰየመ ተብሎ የ2002 ምርጫ ነገር በዚሁ ይጠናቀቃ
ል።

ይህ የቦይኮቱ ጥሪ "አድማጭ" ያጣበት ሁኔታ ከቀጣዩ ትግል አንፃር እንዴት ይታያል? በኔ ግምት ምንም ላናገ
ኝበት "ተቃዋሚዎች የቦይኮት ጥሪ አድርገው ህዝቡ አልተቀበላቸውም፣ 99% ወጥቶ ለኛም ለሰከኑ ተቃዋሚዎችም ድ
ምፁን ሰጥቶ አክራሪዎቹ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ብቸኛ እንደሆኑ ተረጋገጠ" ለሚል የኢህአዴግና የታማኝ ተቃዋሚዎ
ች ፕሮፓጋንዳ የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጠራል። እርግጥ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ ህዝባችን ያለውን እውነታ ስለ
ሚያውቀው ይህ ፕሮፓጋንዳ ምንም ተቀባይነት አይኖረውም። ይህም ሆኖ እንዲህ አይነቱ ውጤቱ የማይታይ ጥሪ "መ
ክሸፉ" በህብረተሰቡ ውስጥ ትንሽም ቢሆን የተስፋ መቁረጥንና የትጥቅ መፍታትን ሂደት ሊያግዝ ይችላል። በየትም
ብንሄድ በየት ግን የቦይኮት ጥሪ ለቀጣዩ ትግል ከአሁኑ ይበልጥ የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ይመ
ስለኛል።

ለ/ ሁለተኛው አማራጭ በምርጫው ሂደት እስከ መጨረሻ መሳተፍ። ይህ ራሱ ሁለት አማራጮች አሉት። በ
አንድ በኩል በያለበት ድምፅ መስጠትና ቆጠራው ሂደት ላይ የተፈጠሩትን ህገ ወጥ ድርጊቶች ተቃውሞና የምርጫው
ን ውጤት አልቀበልም ብሎ የተንዛዛ የፍርድ ቤት ሂደት ውስጥ መግባት ከዚህም አልፎ እንደ ግንቦት ማግስት (ግን ከዚ
ያን ጊዜ ይበልጥ በተደራጀና ቀጣይነት በሚኖረው እንቅስቃሴ) ውጤቱን ህዝብን ይዞ መቃወም። ጥያቄው ይህ ይቻላል
ወይ? እንዴት? የሚል ይሆናል። ሌላው አማራጭ ይህንን ትቶ ኢህአዴግ ለተቃዋሚዎች የቆረጠውን የመቀመጫ ልክ
ተቀብሎ ፓርላማ መግባት። በምርጫው ዘመቻ ወቅት ይከናወኑ ያምንላቸው (ዝቅ ተብሎ የሚወሱት) ጥንድ ተግባራት
በሚገባ ከተከናወኑና ዴሞክራቶች "ምርጫው በመጭበርበሩ...." በሚል መንፈስ እነዚህ አማራጮች ተነጥቀዋልና ቀጣዩ
ን ምርጫ ሳትጠብቅ ትግልህን ቀጥል ለማለት የተሰናዱ ከሆነ ይህ በምርጫው እስከመጨረሻው የሚለው አካሄድና በ
ኢህአዴግ ፓርላሜንት መግባት በዘመቻው ወቅት የተባለውን ሁሉ የሚሽር፣ በዘመቻው ወቅት የተቀሰቀሰውን እምርታ
የሚሰብር፣ ህዝባችንን መልሶ ወደ ተስፋ መቁረጥ የሚመራ በአጭሩ በቀጣዩ ትግል ላይ አሉታዊ ጫና የሚያመጣ አካ
ሄድ ነው። በተለይ እንደ ኢዴፓ አይነቶቹ "ተቃዋሚዎች" ለተቃዋሚው ተሰጠ በሚባለው የመቀመጫ ልክ የአንበሳ
ድርሻ የሚያገኙበትና "የፓርላሜንታዊው ተቃውሞ መሪዎች" ተብለው በሚሰየሙበት ሁኔታ ሃቀኛ ዴሞክራቶች "ነፃ
ምርጫ አይደለም" ከአሉ በሁዋላ በዚህ ውጤቱ ከወዲሁ በታወቀ ምርጫ እስከ መጨረሻው መሳተፍ ለትግሉ ምንም
ርባና ያለው ነገር የሚያመጣ አይመስለኝም።

ሐ/ ሶስተኛው አማራጭ የምርጫው ዘመቻ ተሳትፎ መጨረሻ ደቂቃ ላይ ቦይኮት ማድረግ። ይህ አማራጭ እ
ንደ ግንቦት 97ቱ ባይሆንም ቢያንስ ቢያንስ በዚያን ሰሞን ከሌሎቹ "አዘቦት ወራት" ሻል ያለ የመቀስቀሻ እድል እንደሚ
ሰጥ ጥርጥር የለውም። በመሆኑም ከዳር እስከዳር "የፖለቲካው ስፔስ ጠበበ" እየተባለ በሚተችበት ህብረተሰብ ውስጥ
ይህንን እድል ላለማባከን ባይሆን ምርጫውን እንጂ ዘመቻውን ቦይኮት አለማድረግ የተሻለ አማራጭ ይመስለኛል። ይ

ህንን ከመረጥን ዋና ጥያቄ የሚሆነው በዚህ ተሳትፎ የምንንቀሳቀስባቸው ቴሞች ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው። ተሳትፎው ትንሽም ቢሆን ለትግሉ አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዲኖረው እነዚህ ቴሞች ከሁለት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ።

አንደኛ ነፃ ምርጫ እንዲሆን እነዚህ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች መፐላት ይኖርባቸዋል እነዚህ ካልተፐሉ አንሳ ተፍም እያሉ ከኢህአዴግ ጋር ከመደራደር ይልቅ ፊታችንን ወደ ህዝቡ አዙረን ያለፈውን ምርጫ ግድፈቶች እየጠቆሙ ድምፅህ እንዲከበር ይያ ይያ መሆን ይኖርበታል። ይህ እስካልተፐላ ድረስ በሃገራችን ነፃ ምርጫ ሊካሄድ አይችልም በሚለው ሃሳብ ዙሪያ እስከ መጨረሻው ድረስ ቅስቀሳ ማካሄድ ያስፈልጋል።

ሁለተኛ በምርጫው ዘመቻ የሚደረገው ተሳትፎ ለቀጣዩ ትግል አወንታዊ ሚና እንዲኖረው ለማድረግ የተቃዋሚዎች ቅስቀሳ በነፃ ምርጫ መስፈርቶች ዙሪያ ከመቃኘት አልፎ መሄድ ይኖርበታል። የተቃዋሚዎች ተሳትፎ "ነፃ ምርጫ ቢደረግ ኖሮ" ህዝባችን ያገኝ የነበረውን፣ ነፃ ምርጫ ካልተደረገ ደግሞ የሚያጣውን በግልፅ የሚያሳይ ለህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች አማራጭ ፖሊሲዎችን በማቅረብ ዙሪያ መቃኘት ይኖርበታል። በዚህ ከተስማማን ለገበሬው፣ ለሰራተኛው፣ ለነጋዴው፣ ለስራ አጡ፣ ለወጣቱ፣ ለጎዳና ተዳዳሪው፣ ለከተሜው ድሃ ወዘተ በአጭሩ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ቀላልና ተጨባጭ አማራጮች በማቅረብ ቅስቀሳዎች - ህዝባዊ ስብሰባዎች ወዘተ ማካሄድ ይኖርብናል ማለት ነው።

የዚህ አካሄድ ጥቅሙ ምንድን ነው? ሰላማዊ ህዝባዊ ትግል ካልነው ስትራቴጂ ጋር የሚሄድ ሁሉም እንደብሶቱ፣ ሁሉም ብሶትህ ብሶቴ ብሎና ሁሉም ለዘላቂ መፍትሄ ዴሞክራሲ በሚለው ጥያቄ በአንድ አቅጣጫ እንዲነሳ የሚያግዝ አካሄድ ነው። ትግሉ ዛሬ ቢፈዝ አንዱ ምክንያት ግንቦት 97 ለህዝባችን አቅርበናቸው በነበሩትና ከህዝባችን ድምፅ ጋር በተዘረፉት በጎ አማራጮች ዙሪያ ባለመንቀሳቀሳችንና እነዚህ በጎ አማራጮች ጨርሰው ከኛም አጀንዳ ከህዝባችንም አእምሮ ስለወጡ ነው። በዘመቻው በመሳተፍ እነዚህ ዛሬ ጨርሰው የተረሱት በጎና ህዝባዊ አማራጮች መልሰው በህዝቡ አእምሮ የሚያንሰራሩበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ ከተደረገ ደግሞ የግንቦቱን ስህተት ሳንደግም በቀጣዩ ወቅት የሚዘረፈው ድምፁ ብቻ ሳይሆን እነዚህ በጎ አማራጮችም እንደሆኑ በሚገባ ለማስጨበጥና እነዚህ በጎ አማራጮች በምርጫ ሳይሆን ለዴሞክራሲ በሚደረገው ህዝባዊ ትግል ብቻ እንደሚገኙ እያሰመርን መንቀሳቀስ የሚቻልበት ሁኔታ እናመቻቻለን ማለት ነው።

የኢህአዴግ መንግስት የቦይኮት ጥሪ አይፈራውም። ከላይ እንደተባለው ህዝቡ ነቅሎ ወጥቶ ድምፅ ስለሚሰጥ። ይህኛውን ጥንድ ይዘት ያለው የዘመቻ ተሳትፎ ለማደናቀፍ ግን የማይፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም። ስፍር ቁጥር የሌላቸው እንቅፋቶች ይፈጥራል። በኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ በአለም አቀፍ ኮሙኒቲውም ፊት ይበልጥ መጋለጥን መርጦ ህዝባዊ ስብሰባዎችን፣ ሰልፎችን ወዘተ እስከ መከልከልና በአጭሩ የተቃዋሚ ሃይሎችን የምርጫ ዘመቻ ለማገድ ይሞክራል። ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አማራጮች ብለን ለምሳሌ ለወጣቱ ስራ አጥ የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብና ከወጣቱ ስራ አጥ ጋር ለመመካከር በዚህ ርእስ የአዳራሽ ስብሰባ መጥራት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ግን ኢህአዴግ እንዲህ አይነቱን ስብሰባ ቢፈቅድ/ቢከለክልም ችግር ላይ የሚወድቅበት ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው።

## ሁለተኛ ጥያቄ - እንዴት ነው የምንንቀሳቀሰው?

በምርጫ 97 ወቅት የያዝነውን አቋዋም ብንይዝ፣ የፈለግነውን የትግል ጥሪ ብናደርግ በዚያው በሃገር ውስጥ በህጋዊነት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ሃይል ነበረን። ስብሰባ፣ ሰላማዊ ሰልፎች፣ ጉባኤዎች በስማችን የሚጠሩበት፣ አማራጭ ፕሮግራም በስማችን የሚሰራጭበት ሁኔታ ነበር። ዛሬ ይህ ሁኔታ የለም።

በውጭ አገር በተለይ በዲፕሎማሲው መስክ ይህንን ሂደት በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ፊት ተአማኒነት ለማሳጣት የኢህአዴግ መንግስት ምርጫ ተብየ ነገር በዚህ ጉዳይ አለም አቀፍ መስፈርቶች ጨርሶ የማያሙዋላ እንደሆነ በአንድ በኩል በተጨባጭ ሰነዶች እያስደገፉና በሌላ በኩል ደግሞ በዘመቻው፣ በድምፅ ቆጠራው ወቅት የሚፈፀሙትን ፀረ ዴሞክራሲ ድርጊቶች እያጎሉ ቅስቀሳ ማካሄድ ይቻላል። ይህ ጊዜና የሰው ሃይል ይጠይቃል እ-ንጂ ም-ንም- ች-ግር የለ ውም።

ዋናው መመለስ ያለበት ጥያቄ የወሰድነው አቋዋም በሃገር ቤት እንዴት ይስተጋባል? የሚለው ነው። ይህ ጉዳይ ሰፊ ውይይት ያስፈልገዋል። ለጊዜው የሚታዩኝ በአማራጭነት ሊቀርቡ የሚችሉ ሃሳቦች

1. በአገር ቤት የተመዘገቡ የህብረቱ አባል ድርጅቶች በሁላችንም ስም እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ። ይህ ራሱ ሌ ሎች ጥያቄዎችን ያስነሳል። ህብረቱ ሃገር ውስጥ ህጋዊ ህልውና ስለሌለው በሱ ስም መንቀሳቀስ አስቸጋሪ ይሆናል። በ ሌላ በኩል ደግሞ አሁን ባለው ሁኔታና በያዝነው አቋዋም የተነሳ በህጋዊነት ተመዝግበን እንንቀሳቀስ ማለት አስቸጋሪ ይ ሆናል።

2. በሆነ ሌላ ስም ተመዝግቦ የኛን አቋዋም የሚያስተጋባ ህጋዊ ድርጅት እንዲወዳደር ማድረግ። ይህ አማራጭ ከምርጫው ወቅት ባሻገር ለሚደረገው ትግል የተመቻቸ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። ነገር ግን በአጭ-ር ጊዜ ውስጥ የኢ ህአዴግ የስለላ መረብ ድርጅቱ የህብረቱ ሽፋን መሆኑን ሲደርስበት አመራሩ አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል።

3. ይቻላልን በህቡእ በማሰራጨት ከላይ በዘመቻው ወቅት እንንቀሳሰባቸው ባልናቸው ቴሞች ላይ በተከታታይ አቅጣጫ የሚሰጡና ለውድድር የገቡ ተቃዋሚዎች በነዚህ ቴሞች አንፃር በህዝብ ፊት አቋዋም እንዲይዙ የሚወተው ቱ በራሪዎች መበተን። ይህም አሰራር ከምርጫው በሁዋላ ለሚደረገው ትግል "በምርጫው ዘመቻ ወቅት ይህንን ብለን ነበር...." በሚል መልክ ቅስቀሳችንን ለመቀጠል፣ በምርጫው ሂደትና ውጤት ተስፋ የቆረጠውን ህዝብ ለመቀስቀስና በ ውጭም በውስጥም ደጋፊዎች ለመሰብሰብ የተመቻቸ ሁኔታ ሊፈጥርልን ይችላል።

4. የሚቻለውን ያህል የምንይዘውን አቋዋም በህጋዊ ጋዜጦች ለማሰራጨት መሞከር። ከላይ የጠቀስናቸውን ጥ ንድ የቅ-ስቀሳ ቴሞች በተመለከተ አንደኛ ስለ ነፃ ምርጫ አለም አቀፋዊ መስፈርቶች ከዚህ በፊት በፓሪስ ሁለት ያወጣ ነውን "የዴሞክራሲ ሂደትና የነፃ ምርጫ ትልም" የሚለውን ሰነድ ግንቦት 97 ከተደረጉትና አሁንም በተያዘው ዘመቻ የ ሚታዩትን ግድፈቶች አጉልተው የሚያሳዩ ፅሁፎች በተከታታይ ሊወጡ ይችላሉ። እነዚህ ካልተሙዋሉ ነፃ ምርጫ አ ይቻልም በሚል መንፈስ። ሁለተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችን በተመለከተ በየመስኩ ላሉ ችግሮች በምርጫ 97 ወቅት ከቀረበው አማራጭ ሰነዳችን እየተነሳን እንደዚሁ ተከታታይ ፅሁፎችን ማቅረብ እንችላለን።

እንደ መደምደሚያ

በነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ላይ ጥራት ያለው አቋዋም ከያዝን በሁዋላ ሌላ ውና ሆኖ የሚቀርበው ጥያቄ በዚህ አ ቋዋም ተመርኩዘን በተለይ በዲያስፖራው ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ ሌሎች ስብስቦች ጋር መደራደርና በተስማ ማንባቸው ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመንቀሳቀስ መሞከር ይኖርብናል። ይህ በተለይ የሁሉን አቀፍ ጉባኤንም ጉዳይ የሚመ ለከት ነው። የውይይት መንደርደሪያ ሃሳብ እንዳቀርብ የተጠየቅሁት ሁለተኛው የአጀንዳ ነጥብ ይህ ነው። በዚህ ደግ ሞ ያሉትን ነጥቦች በሚቀጥለው ጊዜ አቀርባለሁ።

ነገደ
02/07/09